# የስድስተኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ የሞዴል ፈተና መለማመጃ ጥያቄዎች

## ቁጥር አንድ

1. ሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑ ልዩ ቁሶች አካላዊ በሆነ መንገድ የሚፈጥሩት የልዩ ቁስ ዐይነት ምን ይባላል?

ሀ) አየር   ለ) ድብልቅ   ሐ) ልዩ ቁስ   መ) ውሃድ

2. የደም ህዋስ የሆነው የትኛው ነው ?

ሀ) ቀይ የደም ህዋስ   ለ) ነጭ የደም ህዋስ   ሐ) ፕሌትሌት   መ) ሁሉም

3. ካርቦንዳያክሳይድ በኢ_ምጋት የአየር ምንሽር ወቅት ስንት በመቶ ይሆናል?

ሀ) 0.03   ለ) 3   ሐ) 4   መ) 0.04

4. በድብልቅ ውስጥ ያሉትን ምንሽሮች በዓይን ወይም በአጉሊ መነፅር በመታገዝ ለይተን ማየት የማንችል ከሆነ ድብልቁ ምን ይባላል?

ሀ) ልይ ዘር   ለ) ዋህድ ዘር   ሐ) ሀ እና ለ   መ) መ/የለም

5. ............... ማለት ሁለትና ካዚያ በላይ ፈሳሾችን በድብልቅ ውስጥ ባላቸው የነጥብ ፍሌት ልዩነት የምናይበት ዘዴ ነው

ሀ) ንጥረት   ለ) ትነት   ሐ) ቀረራ   መ) ጥሊያ

6. ከሚከተሉት አንዱ ባለ ትንቧ ለሚገባውና ለሚወጣው አየር መተላለፊያ ነው

ሀ) ዐቢይ ትንቧ   ለ) ደቂቅ ትንቧ   ሐ) ትንከረት   መ) ሰርን

7. ወደ ውስጥ ስንተነፍስ አየር ወደ ሳንባችን ለመድረስ የሚያልፍባቸው የመተንፈሻ አካላት በቅደም ተከተል ሲቀመጥ ትክክል የሆነው የቱ ነው ?

ሀ) የአፍንጫ ቀዳዳ ⟶ ሰርን ⟶ ድኅረ አፍ ⟶ ዐቢይ ትንቧ ⟶ ደቂቃ ትንቧ

ለ) የአፍንጫ ቀዳዳ ⟶ ድኅረ አፍ ⟶ ሰርን ⟶ ደቂቃ ትንቧ፣⟶ ዐቢይ ትንቧ፣ ⟶ ትንከረት

ሐ) ሰርን ⟶ ድኅረ አፍ ⟶ የአፍንጫ ቀዳዳ ⟶ ደቂቃ ትንቧ፣ ⟶ ዐቢይ ትንቧ

መ) ድኅረ አፍ ⟶ የአፍንጫ ቀዳዳ ⟶ ሰርን ⟶ ደቂቃ ትንቧ፣ ⟶ ዐቢይ ትንቧ

8. የፎቅ ደረጃ ለመውጣት የምንጠቀምበት የቀላል መኪና የ............... ምሳሌ ነው

ሀ) ሸብልቅ   ለ) ዘንበይ ወለል   ሐ) መፈንቅል   መ) ሽክርክሪት

9. በኢትዮጵያና በኬንያ ከፍተኛ ቦታዎች የሚገኘው የዝናብ ዓይነት ምን ይባላል?

ሀ) ግንባር ዝናብ   ለ) ጉባንብ   ሐ) ስግረት   መ) ሳይክሎኒክ

10. የምድር ወገብ አካባቢ ያሉ የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት ዝናብ የሚያገኙት መቼ ነው ?

ሀ) ከሚያዝያ እስከ መስከረም   ለ) ከታህሳስ እስከ የካቲት

ሐ) በጥቅምት እና ሚያዚያ   መ) ከሰኔ እስከ መስከረም

LIVEWORKSHEETS

11. ትንሹ የስርዓተ ትንፈሳ ክፍል የቱ ነው ?

ሀ) ሰርን ለ) አፍወና ሐ) ድህረ-አፍ መ) ትንከረት

12. በወንዶች ላይ የማይታይ አካላዊ ለውጥ የቱ ነው ?

ሀ) የደረት መስፋት ሐ) የድምጽ መጎርነን

ለ) የዳሌ መስፋት መ) በፊት ላይ ጸጉር ማብቀል

13. አንድ አካል የመግፋት ወይም የመጎተት ሂደት መን ይባላል ?

ሀ) ጉልበት ለ) ሀይል ሐ) ኒውተን መ) ጁል

14. ቀላል መኪና ላይ ለመኪናዎቹ የምንሰጠው ሀይል ምን ይባላል ?

ሀ) ክብደት ለ) ዘንግ ሐ) ጥረት መ) ጉልበት

15. ልዩ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ) መቀስ ለ) ቶዮታ መኪና ሐ) ምላጭ መ) ሚስማር

16. የአየር ንብረት ተቆጣጣሪ ያልሆነው የቱ ነው ?

ሀ) ኬክሮስ ለ) ከፍታ ሐ) የሙቀት መጠን መ) የውቅያኖስ ሞገድ

17. በተፈጥሮ ጋዝ የሚታወቀው የምስራቅ አፍሪካ ሀገር የቱ ነው?

ሀ) ኢትዮጵያ ለ) ታንዛን ያ ሐ) ኬን ያ መ) ሶማሊያ

18. ከሚከተሉት አንዱ የስራዓተ ትንፈሳ ጠቀሜታ ነው ?

ሀ) ለማውራት ለ) ለመሽተት ሐ) ቆሻሻ ለማስወገድ መ) ሁሉም

19. ከሚከተሉት አንዱ በወር አበባ ጊዜ የሚከሰት ሂደት ነው?

ሀ) የመህፅን ግድግዳ መፈራረስ ለ) የእንቁላል ከዕንቁልጢ መውጣት

ሐ) የማህፅን ግድግዳ በደም ስሮች መደራጀት መ) ሁሉም

20. ሰዎች ለግል ፍላጎታቸውና ጥቅማቸው ብለው በሌሎች ሰዎች ላይ ጾታን መሰረት ያደረገ ትንኮሳና አስገድዶ መድፈር

.............ይባላል፡፡

ሀ) ጉርምስና ለ) ኮረዳነት ሐ) ጾታዊ ጥቃት መ) ጾታ

LIVEWORKSHEETS

21. ናፍጣን ከድፍድፍ ነዳጅ የምንለይበት የመለያ ዘዴ የትኛው ነው?

ሀ) ንጥረት　　ለ) ትነት　　ሐ) ጥሊያ　　መ) ቀረራ

22. …………ማለት በተወሰነ የዕድሜ ክልል ውስጥ በወንዶችና በሴቶች ላይ የሚከሰት የአካልና የባህርይ ለውጥ ነው፡፡

ሀ) ጉርምስና　　ለ) ኮረዳነት　　ሐ) የወር አበባ　　መ) ሀ እና ለ

23. አንድን ነገር ለሁለት ለመክፈል የሚረዳ ቀላል መሳርያ ነው ፡፡

ሀ) ዘንባይ ወለል　　ለ) ሽብልቅ　　ሐ) መፈንቀል　　መ) መፍቻ

24. በመሬት ላይ የሙቀት ፣ የነፋስ፣ የዝናብ እና የአየር ግፊት ስርጭት እኩል እንዳይሆን የሚያደርጉ ተፈጥሯዊ ምክኛቶች ………..።

ይባላሉ፡፡

ሀ) የአየር ንብረት ተቆጣጣሪዎች　　ለ) የደጋ የአየር ንብረት

ሐ) የሐሩር የአየር ንብረት　　መ) የበረሃ የአየር ንብረት

25. በመጠናቸው በጣም ትንሽ የሆኑ ክብ ቅርጽ ያላቸው ሰውነታችን ሲደማ ብዙ ደም እንዳይፈስ ለማርጋት ይጠቅማሉ፡፡

ሀ) ነጭ የደም ህዋስ　　ለ) ፕሌትሌቶች　　ሐ) ቀይ የደም ህዋስ　　መ) ሁሉም

26. የልብ ትርታን የምናዳምጥበት መሳርያ ምን ይባላል?

ሀ) ቴሊስኮፕ　　ለ) ማይክሮስኮፕ　　ሐ) ስቴቶስኮፕ　　መ) መልስ የለም

27. ከሚከተሉት ውስጥ ልዩ የሆነው የቱ ነው?

ሀ) የደረት መፍፋት　　ለ) የዳሌ መስፋት

ሐ) የድምጽ መጎርነን　　መ) በፊት ላይ ፅጉር ማብቀል

28. ………….. ማለት ኦክስጂን ወደ ሰውነታችን ውስጥ የማስገባትና ካርበንዳይ ኦክሳይድን ወደ ውጭ የማስወጣት ሂደት ነው፡፡

ሀ) ሥራዓተ ልመት　　ለ) ትንፈሳ　　ሐ) የልብ ምት　　መ) ትርታ

29. ከሚከተሉት አንዱ ውኃና አልሚ ምግብን የሚይዝ የደም ክፍል ነው

ሀ) ደም　　ለ) የደም ህዋስ　　ሐ) የደም ዑደት　　መ) ፕላዝማ

30. ከሚከተሉት አንዱ ከደም ስር ዓይነቶች ውስጥ አይመደብም ፡፡

ሀ) ቀይ የደም ህዋስ　　ለ) ደም ቅዳ　　ሐ) ደም መልስ　　መ) ሁሉም

LIVEWORKSHEETS

31. ................. በየ 28 ቀናት በማህፀን በእንቁልጢ ውስጥ የሚካሄድ ተፈጥሯዊ ክስተት ነው፡፡

ሀ) ኮረዳነት ለ) የወር አበባ ሐ) ጉርምስና መ) ሀ እና ለ

32. በሳንባ ውስጥ የሚካሄድ የአየር ልውውጥ ምን ይባላል?

ሀ) ትንፋሽ ለ) ትንፈሳ ሐ) ሳንባ መ) የሳንባ ኡደት

33. ከሚከተሉት አንዱ ስለአየር መገለጫ እውነት አይደለም፤

ሀ) የተለያዩ ጋዞች ተደባልቀው የሚፈጥሩት ልዩ ቁስ ነው፤

ለ) ያለ አየር በህይወት መኖር አይቻልም

ሐ) የአየር ልውውጥ በሳንባ ውስጥ ይካሄዳል

መ) መልስ የለም

34. ................ የአየር እና ምግብ በጋራ የሚተላለፍበት የስርዓተ ትንፈስ አካል ነው፡፡

ሀ) ትንከረት ለ) ደቂቅ ትንቧ ሐ) ባላትንቧ መ) ድህረ አፍ

35. ከሚከተሉት ውስጥ ስለ ምጋት እና ኢ ምጋት ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ) የውሃ ትነት በምጋት ፤ ዝቅተኛ በኢምጋት ከፍተኛ ለ) ሙቀት በምጋት ዝቅተኛ፣ በኢምጋት ከፍተኛ

ሐ) ሙቀት በምጋት ከፍተኛ፣ በኢምጋት ከፍተኛ መ) ናይትሮጅን በምጋት 78% ፤ በኢምጋት 78 %

36. ሁልጊዜ ያለማቋረጥ በስራ ላይ የሚገኘው የሰውነታችን ክፍል የቱ ነው?

ሀ) ሳንባ ለ) ልብ ሐ) አፍ መ) አይን

37. የትኛው የስር ዓተ ትንፈሳ ክፍል ነው ቅርጹን በመቀያየር ሳንባችን በስር ዓት እንድንተነፍስ የሚያስችለው?

ሀ) ድልሺ ለ) ሰርን ሐ) ትንከለት መ) አፍወና

38. በኤርትራ እና በሶማሊያ በስፋት ያለው ንብረት ክልል የትኛው ነው?

ሀ) የደጋ የአየር ንብረት ክልል ለ) የሣር ምድር የአየር ንብረት ክልል

ሐ) የሐሩር ጥቅጥቅ ደን የአየር ንብረት ክልል መ) የበረሃ የአየር ንብረት ክልል

39. ............... በቀላሉ ሊተኩ ወይም ሊታደሱ የማይችሉ የጉልበት ምንጮች ናቸው፡፡

ሀ) ታዳሽ ጉልበት ምንጭ ለ) ታዳሽ ያልሆነ የጉልበት ምንጭ

ሐ) ሀ እና ለ መ) ሁሉም

40. ................. ለጅም የእንጨት ወይም የብረት ዘንግ ሲሆን ድጋፍ በመጠወም ድንጋይ ለመንፈቀል ወይም ሚስማርን በመዶሻ ለመንቀል ይጠቅማል

ሀ) ዘንባይ ወለል ለ) ሽከርከሪት እና ዘንግ ሐ) መፈንቅል መ) ሽከርከሪት

LIVEWORKSHEETS